# የሻደይ በዓል ባህላዊ እሴትና የቀጣይነት ተስፋ

ባህል የአንድ ሕዝብ የታሪክ ትውስታ፣ የእሴት ማስተላለፊያ፣ የማንነት መገለጫና የትውልድ ትስስር መሠረት ነው። ባህላዊ በዓላት ደግሞ እነዚህን እሴቶች ከትውልድ ወደ ትውልድ በተግባር የሚያስተላልፉ ሕያው የባህል ተቋማት ናቸው። ከእነዚህ የማንነትና የባህል መገለጫዎች መካከል የዋግ ኽምራ አካባቢ የሻደይ በዓል አንዱ ነው።

የሻደይ በዓል ሃይማኖታዊ ትርጉምን፣ ባህላዊ ጨዋታን፣ የሴቶችን ተሳትፎ፣ ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦችን፣ የአካባቢ ተፈጥሮ ሀብትንና የማህበረሰብ መስተጋብርን በአንድ ላይ ያጣመረ ልዩ የባህል ቅርስ ነው። ስለዚህ ሻደይን እንደ አንድ የዓመት በዓል ብቻ መመልከት በበዓሉ ውስጥ ያሉትን ሰፊ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ቱሪዝም እሴቶች መዘንጋት ይሆናል።

የሻደይ በዓል ታሪክ በዋግ፣ ላስታ፣ ትግራይ እና ራያና ቆቦ አካባቢዎች ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ አጀማመሩም በተለይ ከቤተክርስቲያን ትውፊትና ከቅድስት ድንግል ማርያም ገድላት ጋር ይያያዛል። በዓሉ የፍልሰታ ጾም መፈታትን ተከትሎ በነሐሴ 16 ቀን የሚከበር ሲሆን፣ “ፍልሰታ” የሚለውም የግእዝ ቃል “መፍለሷ” የሚለውን ትርጉም ይይዛል።

የበዓሉ ሃይማኖታዊ ትርጉም ከእመቤታችን ጋር በሚያያዝበት አተራረክ ብቻ የሚወሰን አይደለም። በሻደይ አከባበር የሚታየው የልምላሜ፣ የተስፋና የመዳን ምሳሌያዊ ትርጉም ከኖህ መርከብና ከኖህ ርግብ ያመጣችው ለምለም ቅጠል ጋርም እንደሚያያዝ በባህሉ ትርክት ይቀርባል። በዚህ አተራረክ የሻደይ ቅጠል የሕይወትና የልምላሜ ምልክት ሲሆን፣ የልጃገረዶች መሽከርከርና ጨዋታም ምሳሌያዊ ትርጉም ይሰጠዋል። ከዚህ የሚታየው ሻደይ በዓል አንድ ትርጉም ብቻ የሚይዝ ሳይሆን ሃይማኖት፣ ታሪክ፣ ማህበረሰባዊ ልምድና ተፈጥሮን ያጣመረ የሕዝብ ባህል መሆኑን ነው። የሻደይ በዓል እስከዛሬ ድረስ በማህበረሰቡ ዘንድ ተወዳጅነቱን ጠብቆ የመጣ ሕያው ባህላዊ በዓል ነው። በተለይም ሴቶች፣ ልጃገረዶችና ሕፃናት በነጫጭ ባህላዊ አልባሳት፣ ጌጣጌጦችና የሻደይ ቅጠል በመጠቀም በዓሉን በድምቀት ያከብራሉ።

የሻደይ ጨዋታ የሚካሄደው በዝማሬ፣ በጭፈራ፣ በእልልታና በማህበራዊ ግንኙነት ነው። ተሳታፊዎች በመጀመሪያ ወደ አብያተ ክርስቲያናት በመሄድ የሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ያከናውናሉ፤ ከዚያም ወደ ማህበረሰቡ ቤቶች በመሄድ ይዘምራሉ፣ ይጫወታሉ፣ ይሸለማሉ እና ይመረቃሉ። ይህም በዓሉ የሃይማኖታዊ ሥርዓትን ከማህበረሰባዊ ትስስር ጋር የሚያገናኝ መሆኑን ያሳያል። ሻደይ የዋግ ኽምራ ማህበረሰብ ታሪክና ማንነት ከሚገለጽባቸው ዋና መድረኮች አንዱ ሲሆን የባህላዊ አልባሳት፣ ጌጣጌጦች፣ ዜማዎች፣ የጨዋታ ሥርዓቶችና ተረቶች ለወጣቱ ትውልድ የቀድሞ ትውልድ እውቀትን የሚያስተላልፉ ቁልፍ መሣሪያዎች ናቸው። በተለይም የሴቶችንና የልጃገረዶችን ተሳትፎ በግልጽ የሚያሳይ ባህላዊ መድረክ ነው።

በዓሉ በተገቢው ሁኔታ ከአካባቢ ኢኮኖሚ ጋር ከተሳሰረ ለብዙ የሥራ ዘርፎች ዕድል ይፈጥራል። ባህላዊ ልብስና ጌጣጌጥ አምራቾች፣ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች፣ ምግብ አቅራቢዎች፣ አርሶ አደሮች፣ አስጎብኚዎችና የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪዎች ከበዓሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

ይህ ባህል ከተፈጥሮና ከታሪካዊ መስህቦች ጋር በተቀናጀ መልኩ ከተሰራ ዋግ ኽምራን የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ የሚያግዝ አቅም አለው። የሻዳይ በዓሉ ብቻ ሳይሆን አካባቢው ያሉት ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊና ተፈጥሮአዊ ሀብቶች ከቱሪዝም ሀብት ጋር የተቆራኙ ናቸው። ሌላው ጉዳይ የሻደይ ቅጠል የበዓሉ ዋና ምልክት ከመሆኑ ባሻገር የአካባቢው ተፈጥሯዊ ሀብት ነው። ስለዚህ የበዓሉን ቀጣይነት ማረጋገጥ ማለት ቅጠሉን በመጠቀም ብቻ ሳይሆን የቅጠሉን ዝርያና መኖሪያ አካባቢ መጠበቅ ማለትም ነው።

የሻደይ ባህል ቀጣይነት እንዲኖረው ከተፈለገ ባህሉን በሳይንሳዊ መልኩ መመዝገብ ተገቢ ነው፡ የሻደይ በዓል ታሪክ፣ የጨዋታ ሥርዓት፣ ዜማዎች፣ ቃላት፣ አልባሳት፣ ጌጣጌጦች፣ የበዓሉ ሥነ-ሥርዓትና ተያያዥ ተፈጥሯዊ ሀብቶች በምርምር ተደግፈው በሰነድ፣ በፎቶ፣ በድምጽና በቪዲዮ መመዝገብ አለባቸው። ባህሉ ይበልጥ ለትውልድ እንዲተላለፍ ከተፈለገ የሻደይ ባህል በትምህርት ቤቶች፣ በባህል ማዕከላትና በወጣቶች ማህበራት በኩል ለልጆችና ለወጣቶች ሊተላለፍ ይገባል። የበዓሉን ትርጉም ሳያዛባ ወጣቱ ትውልድ የባህሉ ባለቤት እንዲሆን በዓሉን ከዘመናዊ የመገናኛ መሣሪያዎች ጋር ማገናኘት ያስፈልጋል።

የሻደይ ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጦች እንዳይጠፉ የአካባቢ እደ ጥበብ ባለሙያዎችን በስልጠና፣ በገበያ፣ በፋይናንስና በቴክኖሎጂ መደገፍ ያስፈልጋል። የሻደይ በዓል ዓመታዊ የቱሪዝም ካሌንደር ውስጥ በግልጽ መካተት፣ በሚዲያና በዲጂታል መድረኮች ማስተዋወቅ፣ የባህልና የተፈጥሮ መስህቦችን የሚያጣምሩ የጉብኝት ፕሮግራሞች መዘጋጀት ይገባል። የሻደይ በዓል በቱሪዝም ምርትነት ብቻ እንዳይቀር የጥቅሙ ተጠቃሚ ማህበረሰቡ ራሱ መሆን አለበት። ይህን ለማረጋገጥ አካባቢያዊ ምርቶችን በበዓሉ ገበያ ውስጥ ማሳደግ፣ የአካባቢ ወጣቶችን እንደ አስጎብኚና የባህል አስተላላፊ ማሰልጠን፣ የእደ ጥበብ ምርቶችን ገበያ ማገናኘት እና ከበዓሉ የሚገኘውን ገቢ በአካባቢ ልማት ላይ ማዋል ይገባል። እንደሀገርም ሻደይን እንደ ሀገራዊ የባህል ሀብት በመመልከት የምርምር፣ የሰነድ አያያዝ፣ የቅርስ ጥበቃና የቱሪዝም ማስተዋወቂያ ድጋፍ ማድረግ ይገባል። በክልል ደረጃ ደግሞ በዓሉን ከአካባቢው የልማትና የቱሪዝም ዕቅድ ጋር ማቀናጀት ያስፈልጋል።

በመሆኑም የሻደይ በዓል በዓመት አንድ ጊዜ የሚከበር የጨዋታ በዓል ብቻ ሳይደረግ በውስጡ የታሪክ ትውስታ፣ የሃይማኖት እሴት፣ የሴቶች ተሳትፎ፣ የወጣቶች ማህበራዊ ትስስር፣ የእደ ጥበብ ምርት፣ የቱሪዝም አቅምና የተፈጥሮ ጥበቃ እሴቶች የተጣመረበት ነው። ይሁን እንጂ የባህል ቅርስ በመከበሩ ብቻ አይቀጥልም፤ ሊመዘገብ፣ ሊመረመር፣ ሊሰራበት፣ ሊተዋወቅና ተፈጥሯዊ መሠረቱም ሊጠበቅ ይገባል። በተለይ የሻደይ ቅጠል እንደ በዓሉ ምልክት እና እንደ ብዝሐ ሕይወት አካል በምርምርና በጥበቃ ሊደገፍ ይገባል።

ስለዚህ የሻደይ በዓልን መጠበቅ የቀድሞውን ሁሉ ሳይቀይር መድገም ብቻ ሳይሆን፣ የባህሉን መሠረታዊ እሴት ጠብቆ ለዘመኑ ትውልድ ተስማሚ በሆነ መልኩ ማስቀጠል ነው። መንግሥት የፖሊሲና የመደገፍ ሚናውን፣ ክልሉ የማስተባበርና የልማት ሚናውን፣ ቤተክርስቲያን የትውፊት ጥበቃ ሚናዋን፣ ማህበረሰቡ የባህል ባለቤትነቱን እና ወጣቱ ትውልድ የቀጣይ ተሸካሚነቱን በተቀናጀ መልኩ ካከናወኑ፣ ሻደይ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሕያው ሆኖ ሊቀጥል ይችላል።